======= ኦሮሙማ ማለት ምን ማለት ነው ⁉️==========

ኦ.ፌ.ኮ. የተሰኘው ድርጅት፥ "ኦሮሙማ አትበሉ" የሚል "ትዕዛዝ እና ማስጠንቀቂያ" አዘል መግለጫ ከሰሞኑ አውጥቷል።

በቀለ ገርባና ግብረአበሮቹ ዛሬ እንዲህ ለማስፈራራት ከመጋጋጣቸው ቀደም ብሎ ውታፍ-ነቃዮቹ ደረጄ ሀብተወልድና ፋሲል የኔአለም እንዲሁም የብአዴን ኮልኮሌ ዘገምተኛ "አክቲቪስቶች" ፥ ኦሮሙማ አትበሉ" እያሉ በማያውቁት ነገር ሲዘላብዱ ነበር። ከሁለት አመት በፊትም በዚህ ጉዳይ በሁለት ክፍል ፅሁፎችን አቅርቤ ነበር።

ከሁለት አመት በኋላ ይህ አጀንዳ እንደ አዲስ እየተነሳ በመሆኑ፥ ኦ.ፌ.ኮ ለሚባለው ፋሽስታዊ ድርጅትም ሆነ ማንኛውም "ይመለከተኛል" ለሚል የፋሽስታዊው ኦሮሙማ መንግስት የስውርና የገሃድ ቅጥረኛ መልስ ይሆን ዘንድ የዛሬ ሁለት ዓመት የፃፍሁትን ፅሁፌን በድጋሚ መለጠፍ አስፈልጓል። አዎ‼️ ኦሮሙማ ማለት ከናዚዝምም የከፋ እጅግ አደገኛና መርዘኛ አይዲዮሎጂና የፖለቲካ ፕሮጀክት ነው‼️‼️‼️ ወደ መቃብር እስኪወርድም በየትኛውም መንገድ እንዋጋዋለን‼️‼️‼️ መልካም ንባብ‼️‼️‼️

* ለኦሮሞ ምሁራን ካለኝ አድናቆት አንዱ ምክንያት፥ በኦሮሞ ብሔርተኝነት እና በኦሮሞ ፖለቲካ ዙሪያ ከበቂ በላይ መፅሐፎችን መፃፋቸው ነው። ብዙ ነገሮችን አቅልለውልናል።

ከእነዚህ ምሁራንና የኦሮሞ ብሔርተኝነት ideologue መካከል፥ ኦሮሙማን theorize እና conceptualize በማድረግ ከጥናታዊ ፅሁፍ እስከ መፃህፍት ማሳተም የደረሰው ዶክተር አሰፋ ጃለታ አንዱ ነው።

እ.አ.አ ከኦገስት 1 እስከ ኦገስት 2, 2015 ዓ.ም፥ በዋሽንግተን ዲሲው የሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ አዳራሽ በተደረገው 29ኛው የኦሮሞ የጥናት ማዕከል አመታዊ ኮንፍረንስ ላይ፥ ጥናታዊ ፅሁፎቻቸውን ካቀረቡ የኦሮሞ ምሁራን መካከል "THEORIZING OROMUMMAA" በሚል ርዕስ ባለ40 ገፅ ፅሁፍ ያቀረበው ዶክተር አሰፋ ጃለታ ነው።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከመውጣቱ ስምንት አመት ቀደም ብሎም፥ እ.አ.አ በኤፕሪል 14, 2007 ዓ.ም የኦሮሞ ጥናት ማዕከል በዋሽንግተን ባደረገው የግማሽ-ዓመት ስብሰባ ላይ "Oromo National Political Leadership: Assessing the Past and Mapping the Future" በሚል ርዕስ "ኦሮሙማ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ አብጠርጥሮ የተነተነው ሲሆን፥ ይህንን ፅሁፉንም፥ ከአሜሪካዊው ሔርዉድ ሼፈር ጋር በመሆን፥ "The Journal of Oromo Studies" በተሰኘው የጥናት ማዕከሉ መፅሔት ቅጽ 14, ተራ ቁጥር 1, 2007 ላይ አሳትሞታል።

በዚህም ሳይወሰን፥ "OROMUMMAA: Oromo Culture, Identity and Nationalism" የሚል መፅሐፍም አሳትሟል።

ስለሆነም፥ "ኦሮሙማ" የሚባለው ነገር፥ በኦሮሞ ልሂቃን coined, conceptualized and theorized ተደርጎ በአግባቡ የተተነተነና የተሰነደ ጉዳይ እንጂ፥ ደረጄ ሀብተወልድ የተባለ ኔዘርላንድ የሚኖር ገሪባ እንደሚለፈልፈው፥ "ኢትዮ-360" የተሰኘው ሚዲያ የፈጠረው አይደለም‼️ አልያም ኮልኮሌ ብአዴናዊያን እንደሚሉት፥ "ፅንፈኛ የአማራ ብሔርተኞች" የፈጠርነው አይደለንም‼️ወይም ተላላኪው ፋሲል የኔዓለም " ኦሮሙማ የሚባለው ነገር አይገባኝም" ብሎ የማይጨበጥ የማይዳሰስ አስመስሎ እንደነገረን ያለ ጉዳይ አይደለም‼️ በመሆኑም የኦሮሞ ልሂቃን conceptualize and theorized ወዳደረጉት የኦሮሙማ ትርጉም በቀጥታ እንገባለን።

በኦሮሞ ብሔርተኞች ልሂቃን ትንታኔ መሠረት፥ "ኦሮሙማ" አምስት /5/ እርከኖች አሉት፦

1. መሠረታዊ ኦሮሙማ (Basic or apolitical Oromummaa)
2. ብሔርተኛ የፖለቲካ አይዲዮሎጂ ኦሮሙማ (Nationalist Political Ideology)
3.ህፅበተ-አዕምሮ የመፈፀሚያ ዕውቀቶች ክምችት ኦሮሙማ
4. ብሔራዊ ፕሮጀክት ኦሮሙማ

5. አለማቀፋዊ ተልዕኮ (Global mission) የሰነቀ አለማቀፍ-ኦሮሙማ (Global Orommuma) በመባል ይከፈላል።
የኦሮሞ ብሔርተኛ ልሂቃን አምስቱንም የኦሮሙማ አይነቶችና እሳቤዎች የተነተኑበትን ዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።
1. መሠረታዊ ኦሮሙማ (Basic or apolitical Oromumma)፡-
* "በሌላ ባህል፣ ቋንቋ፣ ወግ ያልተዋጠና የኦሮሞን ቋንቋ፣ ባህል፣ ወግ፣....የሚናገርና manifest የሚያደርግ ማንኛውም የኦሮሞ ተወላጅ፥ መሠረታዊው ኦሮሙማ (basic Oromumma) አለው ማለት ነው" ይለናል ዶክተር አሰፋ ጃለታ "Theorizing Orommuma" በተሰኘው ጥናታዊ ፅሁፉ።
በአጭሩ ይህ "መሠረታዊ ኦሮሙማ" የሚባለው "ኦሮሞነት" በመባል የሚገለፀው፥ ከፖለቲካ ጋር ንክኪ የሌለውና የኦሮሞ ህዝብ መገለጫዬ በሚላቸው በቋንቋ፣ ወግ፣ ባህል፣ ልማድ ......... የሚገለጽ ነው።
- አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆች፥ እኛ "ኦሮሙማ" ስንል፥ የቃሉን ጥሬ ትርጉም ወይም የኦሮሞ ብሔርተኛ ልሂቃን "basic Orommuma" ብለው በሰየሙት ትርጉም ልክ ብቻ በመውሰድ፥ ሰፊውን የኦሮሞ ህዝብ እየተቸን አልያም ጥላቻ በህዝቦች መካከል እየረጨን አስመስለው ሊያቀርቡ ይሞክራሉ። ይህ ፈፅሞ ስህተት ነው‼️‼️‼️ ለሰፊው የኦሮሞ ህዝብና መገለጫ ቋንቋ፣ ባህል፣ወጉና ልማዱ ትልቅ አክብሮት አለን‼️‼️ የትናንትን ታሪክም በዛሬ ሚዛን የማንለካ የፍርድ አዋቂዎቹ ልጆች ነን‼️
2. ብሔርተኛ የፖለቲካ አይዲዮሎጂው ኦሮሙማ (Nationalist Political Ideology)
* ይህ ሁለተኛው እርከን ኦሮሙማ purely political ነው። ራሱን manifest የሚያደርገው ልክ እንደ ፋሽዝም፣ እንደ ናዚዝም አንድ የብሔርተኛ የፖለቲካ አይዲዮሎጂ ሆኖ ነው።
የዚህ አይዲዮሎጂ መሠረታዊ ሀሳብንም ዶክተር አሰፋ ጃለታ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡- "At the second level, Oromummaa is seen as a nationalist ideology that attempts to mobilize the entire Oromo people to restore their national culture, history, identity, language, human dignity, and freedoms that Ethiopian colonialism has destroyed or suppressed for more than a century." ግርድፍ ትርጉሙም "ሁለተኛው እርከን ኦሮሙማ፥ መላው የኦሮሞ ህዝብን በማንቀሳቀስ በኦሮሞ ላይ የተጫነው የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ከመቶ አመታት በላይ ያጠፋውንና የጨቆነውን የኦሮሞን ባህል፣ ታሪክ፣ ማንነት፣ ቋንቋ፣ ሰብአዊ ክብርና ነፃነት ለማስመለስ የሚያገለግል ብሔርተኛ አይዲዮሎጂ ነው"
* አሰፋ ጃለታም ሆነ መሰል የኦሮሞ ልሂቃኖች "ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ናት" የሚለው ትርክታቸው ጭምብሉ ሲገለጥ "አማራ በምኒልክ በኩል ቅኝ ገዢ ነው" ማለታቸው ሲሆን፥ ኦህዴድም የዚህ ትርክት ተጋሪ በመሆኑ፥ በኦህዴድ ተደርሶ ዛሬም በተግባር እየተዘመረ ያለው የኦሮሚያ ክልል ብሔራዊ መዝሙር በኦሮምኛ ቋንቋ እንዲህ የሚል ስንኞችን ይዟል፡-
"Xurii bara dhibba dhiigaan sirraa dhiqnee
Wareegama qaaliin alabaa kee ol qabne
Gammanne gammadii bokkuu deebitannee"
ትርጉሙም፡- "የመቶ ዓመት እድፍ በደማችን አጠብንልሽ፣
በብዙ እልፍ እልቂት ባንዲራሽን ከፍ አደረግን፣
ደስ ብሎናል ደስ ይበልሽ ስልጣንን መልሰን አገኘን።"
=> የአሰፋ ጃለታ የመቶ ዓመት የቅኝ ግዛት ትርክትና ኦህዴድ "የኦሮሚያ ብሔራዊ መዝሙር" ብሎ በቋጠረው ስንኝ ውስጥ ያለው "የመቶ ዓመት እድፍ" ትርጉም አንድና ያው ሲሆን መሠረቱም ከ political oromumma አይዲዮሎጂ የተቀዳ ነው‼️
አሰፋ ጃለታ፥ "nationalist ideology" ነው በማለት የገለፀው "Political ኦሮሙማ" ወይም "2nd level Oromumma" ፥ በዛሬው የአብይ አህመድና ሽመልስ አብዲሳ የሚዘወረው ኦህዴድ-መሩ "ብልፅግና" የሚባለው ጭምብል core ideology መሆኑን ለማወቅ፥ የሽመልስን ንግግሮች ወደኋላ መለስ ብሎ ማየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ኦህዴድ ዘጠነኛ ጉባኤውን በጅማ ከተማ ባደረገ ጊዜ በግላጭ የፖለተካ ርዕዮቱ ኦሮሙማ መሆኑን አውጇል።

ይህ political ideology ደግሞ፡-
ሀ. አማራን በግላጭም በተዘዋዋሪም በቅኝ ገዢነት ፈርጆ ይነሳል፤
ለ. "ቅኝ ገዢ" በሚላት ኢትዮጵያ ላይ revisionist and revanchist state ሆኖ መቀመጥ ይፈልጋል። ይህንንም ለማስፈፀም established የሆነውን የሀገሪቱን የታሪክና የፖለቲካ ትርክት በማፍረስና በራሱ ትርክት በመተካት ላይ መጠመድን ዋነኛ ስራው አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።
*የእኔና መሰል አማራዊያን ወንድሞቼ ሙግትና ፀብም ከዚህ ጠባብ፣ ፋሽስታዊ፣ revisionist, revanchist እና anarchic ከሆነው አይዲዮሎጂ /Political Oromumma/ ጋር ነው። የዚያች ሀገር ዕጣ ፈንታ በዋናነትም የአማራ ህዝብ እንዴት አይነት የህልውና አደጋ እንደተጋረጠበት የምታውቀው ደግሞ ፥ የዚህን ፋሽስታዊ አይዲዮሎጂ መዳረሻ አሰፋ ጃለታ ፍኖተ-ካርታውን በዚህ መልክ ፅፎ፡- "At this level of Oromummaa, Oromo political awareness is transformed into Oromo nationalism and enables Oromo individuals, families, groups, and communities to comprehend the illegitimacy, evilness, and criminality of Ethiopian colonialism and to struggle for their national liberation." በእነአብይ አህመድ መሬት የረገጠ ስራ ሲሰራበት ስታይ ነው።
3. ህፅበተ-አዕምሮ የመፈፀሚያ ዕውቀቶች ክምችት ኦሮሙማ / Oromummaa as repertoire of knowledge
* ናዚዎች በጥላቻ የነቀዘ፥ የዘር ንፅህና /racial purification/ ለመፍጠር ሲነሱ፥ አይሁድን ከከሰሱበትና ካወገዙበት ነገር አንዱ፥ "አይሁዶች ሳይንስንም ይሁን የአብርሆት እሳቤዎችን አቆሽሸዋል" የሚል ሲሆን፥ በአይሁድ "የቆሸሸው" knowledge reservoir መንፃት የሚችለው አይሁዳዊያኑን በአካል በማጥፋትና በናዚ ፍላጎት የተሰፋ Nazi-Science ሲፈጠር እንደሆነ በማመን መፃህፍት ከማቃጠል እስከ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈፅመዋል።
=> በዶክተር አሰፋ ጃለታ አገላለፅ "ሶስተኛ ደረጃው ኦሮሙማ" ተብሎ የተገለፀውም፥ ይህንን ናዚያዊ ፍልስፍና መሠረት አድርጎ የተነሳ ሲሆን፥ ናዚ አይሁዶችን በከሰሰበት ውንጀላ ልክ፥ የኦሮሙማ ስመ-ጥር ideologue የሆኑት እነ አሰፋ ጃለታም "ኢትዮጵያ" በሚል ጭምብል ጋርደው አማራን እንዲህ ሲሉ ይከሰሳሉ፡- "The Oromo people have been chained mentally and psychologically by Ethiopian ignorance, evilness, and darkness that must be smashed by the liberation knowledge of critical Oromo studies, which are based on Oromo indigenous knowledge and human-centric critical knowledge of the world." በመቀጠልም፥ የህሊናና የስነልቦና እስረኛ አደረገን ከሚሉት "የአማራ ድንቁርና፣ ክፋትና ጨለምተኝነት" ነፃ ለመውጣት፣ እንዲሁም "forces of unfreedom" ሲል ከሚያብጠለጥለው የአማራ እሴት (value) ለመጥራት (purification)፥ መፍትሔው ሶስተኛው የኦሮሙማ አይነት ማለትም ህፅበተ-አዕምሮ የመፈፀሚያ ዕውቀቶች ክምችት ኦሮሙማ / Oromummaa as a repertoire of knowledge/ እንደሆነ እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ኦገስት 2, 2015 ዓ.ም፥ በዋሽንግተን ዲሲው የሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ አዳራሽ በተደረገው 29ኛው የኦሮሞ የጥናት ማዕከል አመታዊ ኮንፍረንስ ላይ፥ "THEORIZING OROMUMMAA" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ገፅ 21 እና ገፅ 22 ላይ በግልፅ ያትታል።
በአጭር ቋንቋ፥ "repertoire of knowledge" በሚል በእነ አሰፋ ጃለታ የተገለፀው "ሶስተኛው እርከን ኦሮሙማ" ማለት ፥ የናዚ ፍልስፍና መሠረት ከሆኑት የBernhard Foerster እና የ Alfred Rosenberg ስራዎች በቀጥታ የተቀዳ ፋሽስታዊ እሳቤ ሲሆን የፈጠራ ተረቶችንና ታሪክን በመከለስ አዲስ ሀገራዊ የፖለቲካና የታሪክ ትርክት በመፍጠር የፖለቲካ የበላይነታቸውን ለማስጠበቅ እየሰሩበት ይገኛል‼️‼️‼️
4. ብሔራዊ ፕሮጀክት ኦሮሙማ፡-

* ኦሮሙማን እጅግ አደገኛ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ፥ ከፋሽስታዊ ጠባብ የፖለቲካ አይዲዮሎጂነቱም በላይ፥ አሰፋ ጃለታ በአራተኛ እርከንነት የገለፀው national project መሆኑን ነው።
"ኦሮሙማ" ፥ National project መሆኑ፥ ልክ እንደማንኛውም ፕሮጀክት በየደረጃው መከናወን ያለባቸው
collection of tasks ያሉት ሲሆን በመጨረሻም የእነዚህ ስራዎች ድምር ውጤት የሚያዋልደው distinctive result ይኖረዋል። ይህም ማለት ዛሬ የምናየው በኦሮሚያ የሚፈፀመው የዘር ማጥራት ያልተቋረጠ ዘመቻ፣ አዲስ አበባን የመሰልቀጥ ርብርብ፣ አጎራባች ክልሎችን Oromonized የማድረግ ስራ ሁሉ የፕሮጀክቱ ፍፃሜ የሆነውን ከተቻለ የኦሮሚያ ሪፐብሊክን አለበለዚያም ኦሮሞናይዝድ የተደረገችውን ኢትዮጵያ ለማዋለድ የሚሰሩ collection of tasks ናቸው።
ይህንን ደግሞ የኦሮሞ የጥናት ማዕከል በሚያሳትመው መፅሔት ቅጽ 14, ተራ ቁጥር 1, 2007 ላይ "Oromo National Political Leadership: Assessing the Past and Mapping the Future"
በሚል ርዕስ ባወጣው ፅሁፍ ውስጥ "The Concept of Oromummaa and Identity Formation in
Contemporary Oromo Society" በሚለው ንዑስ-ርዕስ ስር እንዲህ ሲል በግልጽ ነግሮናል፦
"Oromummaa is a complex and dynamic national and global project. As a national project and the master ideology of the Oromo national movement, Oromummaa enables Oromos to retrieve their cultural memories, assess the consequences of Ethiopian colonialism, give voice to their collective grievances, mobilize diverse cultural resources, interlink Oromo personal, interpersonal and collective (national) relationships, and assists in the development of Oromo-centric political strategies and tactics that can mobilize the nation for collective action empowering the people for liberation."
* የአማራ ፖለቲከኛ ነን የሚሉትም ይሁኑ genuinely የሀገሪቱ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ሰዎች ከጥቂቶች በቀር፥ የየዕለት የኦሮሙማው መንግስት የሚያከናውናቸውን collection of tasks የኦሮሙማ-ፕሮጀክት አካልና የፕሮጀክቱ ፍፃሜ ውጤት የኦሮሚያ ሪፐብሊክ አልያም ኦሮሞናይዝድ የሆነች ኢትዮጵያን የመፍጠር አካል አድርጎ የማየቱ ነገር እምብዛም ነው። ይህ አይነቱ myopic interpretation ያተረፈልን ነገር ቢኖር የፋሽስቶቹ force-multiplier መሆንን እና ፕሮጀክታቸውን ያለተግዳሮት ከግብ እንዲያደርሱ በድንቁርና አልያም በሆድ-አደርነት ተባባሪ መሆንን ነው።
* ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር፥ ብዙሃኑ ለፖለቲካ ቅርብ ነኝ የሚለው ህዝብ ኦሮሙማን ፕሮጀክት አድርጎ ከመቀበል ይልቅ ልክ እንደ ዴሞክራሲ፥ ሂደት /Process/ አድርጎ ከማመን አልፎ ቀድመን የነቃነውን "በለውጥ አደናቃፊነት" ለመክሰስ መጋጋጡ ነው። "ኦሮሙማ" Process ቢሆን ኖሮ፥ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ፥ የ Optimization ጉዳይ ስለሚሆን፥ ገንቢ ሃሳብ በማዋጣትና ጊዜ በመስጠት ነገሮችን እንዲሻሻሉ ማድረግ ይቻል ነበር። የሀገሪቱም ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ አዎንታዊ ለውጥ እያሳየ እንጂ እየከፋ ባልሄደ ነበር።
ነገር ግን የኦሮሞ ideologues በጥናታዊ ፅሁፎቻቸው አስረግጠው እንደነገሩን፥ "ኦሮሙማ" Process ሳይሆን distinctive product (የኦሮሚያ ሪፐብሊክን አልያም ኦሮሞናይዝድ የሆነች ኢትዮጵያን) እንዲያዋልድ በቀመር እየተሰራበት ያለ Project ነው‼‼‼
5. አለማቀፋዊ ተልዕኮ (Global mission) የሰነቀ አለማቀፍ-ኦሮሙማ (Global Orommuma)፦
* "ግሎባል ኦሮሙማ" ማለት በአጭሩ፥ ፋሽስት ወያኔ የአማራን ህዝብ በሌሎች ለማስጠላት የሚከተለውን መንገድ መከተል ማለት ነው። አሰፋ ጃለታ "ኢትዮጵያ" በሚል ጭምብል ሽፍኖ "ቅኝ-ገዢ" ባለው አማራ ላይ ሌሎችን እንዴት ማነሳሳት እንዳለባቸው "በግሎባል ኦሮሙማ" ትንታኔው ስር እንዲህ ሲል ፅፏል፦ "Using the philosophy of safuu (moral and ethical order), global

Oromummaa promotes horizontal and democratic relations among all the various peoples who have been colonized and brutalized by the Ethiopian colonial state."
* "ኦሮሙማ" አለማቀፍ ተልዕኮዬ ብሎ የሰነቀው፥ ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችን "የአማራ ቅኝ-አገዛዝ የፈጠረብን common historical trauma እና አማራ የሚባል common historical enemy አለን" በሚል sentiment በመቀስቀስ አማራን የመነጠል ስራ ነው።
* "ኦሮሙማ" ጥላቻን ከመስበክና አማራን አሰይጥኖ ትውልድን ከመመረዝ በዘለለ constructive ideology አይደለም። ለዚህም ነው የኦሮሚያ ሪፐብሊክን የመመስረት ዕድል ቢያገኝ እንኳ አማራን Boogyman አድርጎ Global-Oromumma በሚል ለመቀጠል ዕቅድ ያዘጋጀው። ይህ ደግሞ ከጥላቻ በቀር ለወጡበት ህዝብ አንዳችም ነገር sustainably deliver ማድረግ የማይችሉ Pseudo-ideologies መገለጫ ነው። ሁለት ዓለማቀፍ ምሳሌዎችን እንመልከት።
ከሌኒን ሞት በኋላ በስታሊንና በሊዮን ትሮትስኪ (ወይም በትክክለኛ ስሙ ሌቭ ዴቪዶቪች ብሮንስታይን) መካከል ከነበረው ንትርክ መካከል፥ ትሮትስኪ "ኮሚንዝምን በፍጥነት አለማቀፍ ካላደረግነውና በሶቭየት ብቻ እንዲወሰን ካደረግነው ሲስተሙ dead end ላይ ይደርስና እንፈርሳለን" የሚል ሀሳብ ያቀነቅን ነበር። በእርግጥ የኋላ ኋላ ትሮትስኪን ካስገደለው በኋላም ቢሆን ስታሊንም ሀሳቡን ገዝቶታል። የሆነው ሆኖ በሰባ ዓመት ውስጥ የቱንም ያህል አለማቀፍ ቅርፅ ሊያስይዙት ቢሞክሩም ስርዓቱ dead end ላይ ደርሶ ከስርዓትም በላይ ታላቋን ሀገር ለፍርሰት አጋልጧት አልፏል። በተመሳሳይ በአያቶላህ ክሆሚኒ የተመራው የኢራኑ theocratic fascism ያንን የመሰለ የስንት ሺህ አመታት ስልጣኔና ጥበብ መፍለቂያ የሆነውን ሀገር በ clergy council ተጠርንፎ እንዲያዝ ከማድረጉም በላይ የህልውናው ማስቀጠያ አድርጎ የሚጠቀመው ፀረ-እስራኤል rhetoricን ነው። በእርግጥ ከቃላትም በዘለለ ራሱን የአለማቀፍ የ Shia shrines የበላይ ጠባቂ፣ የኢየሩሳሌም ነፃ አውጪ አድርጎ ከመስበክ አልፎ በሊባኖን፣ ጋዛና የመን ሄዝቦላህ፣ ሀማስና የሁቲ ሚሊሻዎችን አደራጅቶ አሰማርቷቸዋል። በዚህም ሳይወሰን የአያቶላህ አርሚ IRGC አካል የሆነውና Quds የሚባለው expeditionary force ዋነኛ ተልዕኮም በመካከለኛው ምስራቅ የእስራኤልን ከፍ ሲልም የአሜሪካንን ጥቅም destabilize ማድረግ ነው። በነገራችን ላይ የዚህ ኃይል አዛዥ የነበረውና በምዕራቡ ዓለም "The Shadow Commander" በመባል የሚታወቀው ቃሲም ሱሌማኒ (ብ.ጄ/ል)፥ ኢራቅ ባግዳድ የሚገኘውን የአሜሪካ ኤምበሲን በQuds Force እንዲወረር በማድረጉ ምክንያት ትዕግስቱ የተሟጠጠው ዶናልድ ትራምፕ "የይሙት-በቃ" Presidential Order ባሳለፈበት በ24 ሰዓት ውስጥ ነበር እ.አ.አ በጄንዋሪ 03, 2020 ዓ.ም ባግዳድ አለማቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ አቅራቢያ በ Drone ጥቃት የተገደለው።
=> ለማንኛውም ወደተነሳንበት ጉዳይ ስንመለስ፥ የሠርቶአደሩን አምባገነንነት /Proletariat dictatorship/ በማንበር Utopian society እገነባለሁ ብሎ አለማቀፍ የመደብ ጠላት በመፍጠር የተንቀሳቀሰውም ስሁት-ርዕዮት ይሁን ለ12ኛው ኢማም ዳግም መምጣት መንገድ ጠራጊ ነኝ በሚል ሃይማኖታዊ ጭምብል የሚንቀሳቀሰው Theocratic fascist ቡድን፥ ከጥላቻና ተቃርኖን ከመስበክ የዘለለ ለህዝቡ deliver የሚያደርገው sustainable development የለውም። ሥርዓቶቹም መቆሚያ መሠረታቸው አለማቀፍ ጠላት ፍለጋ መማሰንና ለአንዳች global noble cause የቆሙ አስመስሎ ለህዝባቸው በመስበክ ብቻ ነው።
ኦሮሙማም በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ ከእነዚህ ከመከኑ አስተሳሰቦች የተለየ አይደለም፤ ለዚህም ነው ከፅንሰት እስከ ጉልምስና ድረስ lifeblood ሆኖ ያገለግለኛል ብሎ የተማማለበትን የአማራ ጥላቻ በሌሎች ህዝቦች በማስረፅ ለህልውናዬ መቀጠል ዋስትና ይሆነኛል ሲል Global Orommuma የሚል theorization ውስጥ የገባው‼️
* ስለሆነም እኛ "ኦሮሙማ ፋሽስታዊ አመለካከት ነው" ስንል፥ ራሳቸው የኦሮሞ ብሔርተኛ ምሁራን በእርከን ከፋፍለው ካስቀመጡት ውስጥ መርዘኛ ፖለቲካዊ አጀንዳ የያዘውን ፥ ማለትም፦

- Nationalist Political Ideology Oromumma
- "Repertoire of Knowledge" Oromumma
- National Project Oromumma
- Global Orommuma ታሳቢ በማድረግ እንጂ፥ ጎረቤታችችን የሆነውን የኦሮሞን ህዝብ ማለታችን ፈፅሞ አይደለም‼‼‼

ራሳቸው የኦሮሞ ልሂቃኑ የተጠቀሙበትን ስያሜ፣ ሀተታና ትንተና መሠረት በማድረግ ላይ ብቻ ተመስርተን ነው እያወገዝን የምንገኘው። ከማውገዝም በላይ ይህንን ፋሽስታዊ አመለካከት በጠላትነት እስከመጨረሻውም እንደምንዋጋው ጠላትም ወዳጅም ሊያውቀው ግድ ይላል‼‼‼

ዴቭ ዳዊት።